**<u>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆንሱል ጄኔራል ጽ/ቤት ሶማሊለንድ ሐርጌሳ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተጣለበትን 7ኛ አመት በደማቅ ሁኔታ አከብሯል።</u>**

መጋቢት 27 ቀን 2010 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆንሱል ጄኔራል ጽ/ቤት በሶማሊላንድ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር በመሆን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ገድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ የተጣለበትን 7ኛ አመት ክብረ በዓል በድምቀት አክብረዋል። በዓሉን አስመልክቶ የፓናል ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ የፓናል ውይይቱን የመሩት የቆንስል ጄኔራሉ ክቡር ብ/ጄኔራል በርሀ ተስፋይ ሁለት ዋና ሃሳቦችን እንስተዋል።

በመጀመሪያ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የደረሰበትን ደረጃና የህዝቡ ተሳትፎ ህብረተሰቡ በሞራል፣ በገንዘብ እንዲሁም በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ያደረገው ድጋፍ ከፍተኛ እንደነበር ተወስቷል፣ በቀጣይም ግድቡ እስኪጠናቀቅ ድረስ የህብረተሰቡ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጥሪያቸውን አቅርበዋል። በተጨማሪም ግድቡ ሲጠናቀቅ ለአገራችን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንደሚሰጥና ለተፋሰሱ አገራትም ቢሆን ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው አስረድተዋል።

ሁለተኛው ነጥብ፣ በቅርቡ በአገራችን ተከስቶ በነበረው አለመረጋጋት በሶማሊላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊንና ትዉልደ ኢትዮጵያዊን በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ብዥታ ለማጥራት ያለመ ነበር፣ በመሆኑም በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የሪፎርም እንቅስቃሴን በማሳት የህዝባችንን ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እንደሚመለሱ፣ ይሁን እንጂ ህብረተሱ እያነሳ ላለው የልማት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ተገን በማድረግ ጸረ-ሰላም  ኃይሎች የህዝቡን ጥያቄ በመጥለፍ የአገራችን ህገ-መንግስታዊ ስረዓት ለማፍረስ መንቀሳቀሳቸው እንዲሁም ለአገራችን በጎ የማያሰቡ አገራትም ችግሩን ለማባባስ ሞከረዋል፣ ሆኖም አገሪቱን የሚመራው ድርጅት ኢህአዴግና መንግስት ባደረጉት ጥልቅ ግምገማ ህብረተሰቡ የጠየቀውን ጥያቄ ለመመለስ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኝነት በማሳየት ወደ ለውጥ ስራዎች መግባቱን አስረድተዋል፣ እዚህ የሚገኘው ህብረተሰብም ከሚያደናግሩ የጠላት መልዕክቶች እራሱን በመጠበቅ ለአገሩ ደህንነት መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

በመጨረሻም በበዓሉ ላይ በተደረገው የቦንድ ሽያጭ ፕሮግራም ላይ 16,000 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ  የቦንድ ሽያጭ ተካሂዷል።